# የሐራጅ ጨረታ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለአይካ አዲስ ቴክስታይልና ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኃ/የተ/የግል ማህበር ለሰጠው የብድር ገንዘብ አመላለስ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ የተመለከቱትን ንብረቶች በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 98/90 በተሰጠው ስልጣን መሠረት በግልፅ ጨረታ /ሐራጅ/ ለመሸጥ ይፈልጋል::

| የተበዳሪው/የመያዣ ሰጪው ስም | የንብረት ዝርዝር | የንብረት አድራሻ | የሃራጁ መነሻ ዋጋ (በብር) | የሃራጁ ደረጃ | የሃራጁ ቀንና ሠዓት |
|---|---|---|---|---|---|
| አይካ አዲስ ቴክስታይልና ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኃ/የተ/የግል ማህበር | በ 205,000 ሜትር ካሬ በታ ላይ የተቋቋመ የተቀናጀ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ከነሙሉ ግንባታዎች፤ተሽከርካሪዎችን የምርት መሳሪያዎች፤ ፤ልዩ ልዩ መለዋወጫዎች ጥሬ ዕቃና ሙሉ በሙሉ ያለቀለት ምርት ፤ | ሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 08 | 1,824,653,419.32 (አንድ ቢሊዮን ስምንት መቶ ሃያ አራት ሚሊዮን ስደስት መቶ ሀምሳ ሶስት ሺህ አራት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር ከሰላሳ ሁለት ሳንቲም) | የመጀመሪያ | ሐምሌ 16 ቀን 2011 ዓ.ም<br>ከሰዓት 8፡00ሰዓት እስከ 10፡00ሰዓት |

**ማሳሰቢያ ፤**

1. ተጫራቾች የሐራጁን መነሻ ዋጋ 25 በመቶ በባንክ ክፍያ ማዘዣ /ሲ.ፒ.ኦ/ ብቻ በማስያዝ መጫረት ይችላሉ፤
2. አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያሸነፈበትን ቀሪ ገንዘብ በ15 /በአስራ አምስት/ ተከታታይ ቀናት ውስጥ አጠቃሎ ካልከፈለ ያስያዘው ገንዘብ ለባንኩ ገቢ ሆኖ ጨረታው ይሰረዛል። በሐራጁ ለተሸነፉ ተጫራቾች ያስያዙት ክፍያ ማዘዣ /ሲ.ፒ.ኦ/ ወዲያውኑ ተመላሽ ይደረጋል።
3. ሃራጁ የሚካሄደው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው፣ ተበዳሪው እና የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ተወካዮች ብቻ በተገኙበት ሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 08 በሚገኘው የፋብሪካው ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው ::
4. 15% የተጨማሪ እሴት ታክስና ሌሎች ገዢ እንዲከፍላቸው በሕግ የተወሰነ ክፍያዎችን፣ የስም ማዛወሪያ ክፍያን ጨምሮ ገዢው ይከፍላል፤
5. ሐራጁ የሚከናወነው የፋብሪካው ሥራ እየቀጠለ ባለበት ሁኔታ ስለሆነ ከላይ በሠንጠረዥ ከተመለከተው አማካይ ዋጋ ግምት ያላቸውን ጥሬ ዕቃዎች፤በምርት ሂደት ላይ ያሉ ዕቃዎች፤ያለቀላቸው ምርቶች፤በመጋዘዝ ላይ ባሉ ዕቃዎችና መለዋወጫዎች ወዘተ ምክንያት ለውጥ እንደሚኖር የሚጠበቅ ሲሆን በዚህም ለውጥ

ምክንያት በሚኖር ጭማሪዎች ላይ የጨረታው አሸናፊው በርክክብ ወቅት በሚደረስበት የትመና ዋጋ ስሌት መሠረት በጨራታው ካሸነፈበት ዋጋ በተጨማሪ የእነዚህን ንብረቶች ግምት ዋጋ ድምር በጥሬ ገንዘብ/ በዱቤ/ ከፍሎ መውሰድ ይኖርበታል :: ነገር ግን በነዚህ ንብረቶች ሽያጩ ላይ በባንኩና በገዢው መካከል ስምምነት ካልተደረሰ ባንኩ በሚያምቸው መንገድ ንብረቶቹን በቂ ጊዜ ወስዶ ያለምንም ተጨማሪ ወጪ የማንሳት መብት ይኖረዋል::

6. ፋብሪካው(ፕሮጀክቱ) እየሠራ ያለ በመሆኑ ምክንያት ለሥራው ማነቆ የሆኑ ማሽኖችን ለመተካት የተፈጸመ ግዢ ካለ በርክክብ ወቅት በሚደረስበት ግምት ገዢው በአሸነፈበት ዋጋ ላይ ጨምሮ በመክፈል ንብረቱን ይወስዳል።
7. ፕሮጀክቱ ምርቶቹን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ እንደመሆኑ መጠን በሂደት ላይ ያሉ ትዕዛዞች ወይም ድርጅቱ ውል የፈጸመባቸው ነግር ግን ያልላካቸው ምርቶች እስኪላኩ ድረስ ባንኩ ለገዢው ንብረቱን የማስረከብ ሂደት የማዘገየት መብት ይኖረዋል።
8. የፋብሪካው የምርት መሣሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች፣ ወዘተ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው በመሆናቸው ገዢው የቀረጥ ነጻ መብት ሊኖረው አሊያም በመንግስት የሚፈለገውን ቀረጥ ለመክፈል ይገደዳል ::
9. ባንኩ ለሽያጭ የቀረቡትን ንብረቶች የሚሸጠው ከተቻለ ሙሉ በሙሉ በጥሬ ገንዘብ ሲሆን አሸናፊው በባንኩ ብድር ፖሊስ መሠረት አስፈላጊውን መስፈርቶች ካሟላና የፋብሪካውን ሥራ የሚያስቀጥል ከሆነ ንብረቱን በከፊል ብድር ለመግዛት መጠየቅ ይችላል:: ነገር ግን በከፊል ብድር ለመግዛት የጨረታ አሸናፊው በራሱ ስም ወይም እራሱ 10%/አስር በመቶ/ ወይም ከዚያ በላይ የአክሲዮን ባለድርሻ የሆነበት የንግድ ማህበር ከግብር፤ከታክስና ከሌሎች ማናቸውም ዕዳዎች ነፃ መሆኑን ከሚመለከታቸው አካላት ማስረጃ በማቅረብ እንዲሁም ምንም ዓይነት የዕዳ ይከፈለኝ ጥያቄ ያልቀረበበት መሆን አለበት።
10. ዝርዝር እና ተጨማሪ መረጃን በተመለከተ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ዋና መ/ቤት ታወር ሁለት ሦስተኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው የኘሮጀክት ማገገሚያና ብድር ማስመለስ ዳይሬክቶሬት II በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 011-524-53-73 ደውሎ ማግኘት ይቻላል ወይም ከባንኩ ድህረ ገጽ www.dbe.com.et. ማግኘት ይቻላል። ንብረቱን ከዳሬክቶሬቱ ጋር አስቀድሞ ቀጠሮ በመያዝ መጐብኘት ይቻላል፤
11. ባንኩ የተሻለ መንገድ ካገኘ ሐራጁን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**<u>የኢትዮጵያ ልማት ባንክ</u>**